# <u>ምንድነው የጎደለን?</u>

**ከእያዩ ቢወጣ**

ምርጫ እየተቃረበ ነው፣ እነ እገሌ ገቡ እነገሌ ወጡ፣ እነ እገሌ ወደቁ እነ እገሌ ተነሱ፣ የሚለው ትችት፣ እሮሮ፣ ሀዘንና፣ ቁጣ፣ ከምንጊዜውም በበለጠ በተለይም ካለፉት ቀዝቃዛ የፖለቲካ አመታት ወጥተን አሁን ከአንድ ወር ወዲህ ወያኔና አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች የምርጫ ስነምግባር በሚል እራፊ ጨርቅ ተጠቅልለው ከወያኔው-ተጋድሎ ሐርነት ትግራይ__ጋር አብረው ተላልሰው ሸብረክ ካሉ ወዲህ፣ በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች አስተሳሰብና አደረጃጀት ብሎም የትግል ዘዴ ዙሪያ የተሰለፉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ከሞላጎደል በአንድ ድምጽ በስምምነቱና ስምምነቱን በፈረሙት፣ ለመፈረምም ፈራ ተባ በሚሉት በአብዛኛው ጸረ ወያኔ አቋም አላቸው፣ የህዝብ ወገን፣ የትግሉ መሪም የወዳጅ ሀይል ናቸው በማለት ለረጅም ጊዜ፣ ቢያንስ ካለፈው ምርጫ ወዲህ፣ በተለያየ መልክ ድጋፉን ሲለግስ የቆየው በውጪ ሀገር ተበትኖ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ሁሉ፣ በአንድ ድምጽ ማለት ይቻላል፣ አበክሮ በመረረ ድምጽ በቁጣ አንደበት ሌት ተቀን በጋለ መንፈስ ስምምነቱን <u>በፈረመው በመኢአድ</u> ላይና እንደ ማስጠንቀቂያም ሆኖ ተመሳሳይ ጉዞ ለሚከጂሉ ሁሉ እንደማሳሰቢያና የተሳሳተ የፖለቲካ መንገድ መሆኑን አበክሮ እየተወያየና መፈረማቸው ትክክል ባለመሆኑም እየኮነነ ይገኛል።

<u>ለምን ጩኸቱ መረረ? ለምንስ ይህ የፖሊቲካ ቀውስ መጣ?</u>

አሁን ለተፈጠረው የፖለቲካ ውዝግብ ተጠያቂዎቹ መኢአድ ወይም መሰሎቹ ብቻ ሳይሆኑ እኛ ደጋፊዎቹም በበኩላችን ለዚሁ ጥፋት ትልቅ አስተዋጽዖ ማድረጋችንንና ለዚሁም በቅንነት እራሳችንን ከትግሉ አንጻር መርምረን፣ ትግሉ እሰከ አሁን የደረሰበትን ውድቀት ከምን የመጣ እንደሆነ ቆም ብለን መጠየቅና መረዳት ለትግሉ አስተዋጽዖ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን ለታጋይ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችም ለሀሳብ ጥራትና ለመራራ ትግል የበለጠ እንዲዘጋጁ ይረዳል።

አመራሩ የበሰለ እንዲሆን ከታች ያለውንም ተከታይ ማንም አመራር እነደፈለገ የማይፈነጭበት፣ የፈለገውን አቋም ተቀበሉ የማይልበትን ሁኔታ ይፈጠራል። ከታች ወደላይ ከላይ ወደ ታች የሚለው ዴሞክራሲያዊ የድርጅት አሰራር መርህ፣ በተግባር እንዲውልና የተጠናከረ አመራር ከአባላትጋር፣ አባላት ከህዝብ ህዝብም ከድርጅት ጋር ድርና ማግ ሆነው አንዱ በአንዱ ላይ <u>በመተከል (PRINCIPLE) ላይ በተመሰረተ</u> አቋም ተደጋግፈው ትግሉ የጠራና የነጠረ እንዲሆን ማድረጉ ብቻ ሳይሆን የተዋሐደም እንዲሆንና ከብረት የጸና እምነት እንዲኖረው ይረዳል። አባላትና ደጋፊዎች አርጉ የተባሉትን ከማረግ አምጡ የተባሉትን ከመሰንዘር ክቡር ህይወታቸውን ክፈሉ ሲባሉም ያለማመንታት የከፈሉበት በኢትዮጲያ ስም ለኢትዮጲያ ህዝብ የተደረገውንና የሚደረገውን

መስዋትነት አሁን በምናየው የድርጅቶች ቀውስና ውዥንብር ውስጥ ሲገባ

ጥፋቱን በድርጅቶች ላይ አላከን ልናልፈው አንችልም። የትግሉ አካል ነን፣ ትግሉ ይመለከተናል እስካልን ድረስ እስከ አሁን ድረስ ቢያንስ ከ97ቱ (2005) ምርጫ ወዲህ በሰፊው በአገራችን ፖለቲካ ስንገበገብ ቆይተናልና፣ የተለያዩ ድርጅቶች ሲሰሩና ሲፈርሱ፣ እንደ ግራምጣ ተሰንጥቀው ዞር ብለው ደግሞ እንደ አለላ ልዩ ቀለም ተነክረው ሲመጡ እንደ አላየ እንዳልሰማ ሆነን አሆ! ሎጋው ሽቦ! የኢትዮጲያ አንድዬ ልጅ (ኢትዮጲያ አንድ ልጅ ወይም ጥቂት ስመ ጥሩዎችን ብቻ ወልዳ የመከነች ይመስል) በማለት ስናሞካሻቸው፣ ግለሰቦችን በአማልክት ድርጅቶችን ቤተክርስቲያንና በመስጊድ መስለን ይህማ መንፈስ ነው ይህማ ቅዱስ ነው፣ ፍቅር ነው….፣ እንዲያው ለነገሩማ ያልተባሉት

*አባባል ያልተወደሱት ዉዳሴ ያልተዜመላቸው ዜማ ያልተቀኘንላቸው ቅኔ ከቶ አልነበረም፣ ታዲያ ባለፉት 4 አመታት ሲያዘፍኑን የነበሩት ድርጅቶች ሆኑ ግለሰቦች አሁን የት አሉ የት ደረሱ? ለማለትና ለመጠየቅ በጣም አርገን የምንደፍረውን ያህል እራሳችንን በዚያን ያህል ክብድት ለመጠየቅ መነሳት ያለብን ጊዜ ዛሬ ነው።*

*እራሳችንን ለመጠየቅ መነሳት አለብን ብለን ጫና ስናደርግ ሁለት ነገሮች ላይ አጽንኦ ማረግ ያስፈልጋል፣*

1) *ትግሉን በማበረታታትና በመደገፍ አይናችንን ከተጋድሎ ሐርነት ትግራይ ላይ መንቀል የለብንም፣*

2) *የምንደግፋቸውን ድርጅቶች አሁንም በቀና እያስተዋልን ድጋፋችንን እየሰጠን መጠየቅ ያለበትን ጥያቄ መጠየቅ የግድ ነው፣*

*በአጭሩ እራሳችንን እስክናጠራ እስክንመረምር ከሁሉም ነገር እንታገድ የሚል እንደምታ እንዳይኖር ለማለት ነው።*

*ተጋድሎ ሐርነት ህዝብ ትግራይ ወያኔ በሀገራች ላይ ምንጉዳት አደረሰ? አገራችን በምን አይነት አድጋ ላይ ነች? ብሎ ማውራት "ልጅ ለናቷ ምጥ አስተማረች" እንደተባለው በችግሩ ዉስጥ ያለን ህዝብ ስለ ችግር ነጋሪ አንሆንም። ይህን ፅሁፍ የሚዳስስ ማንኛውም ሰው ኢትዮጲያ ያለችበትን አደጋ አያውቅም ብንል ከእውነት እንርቃለንና ወደ ጎደለው እንመለስ።*

*አንድ ህዝብ ከገዥው መንግስት ጋር የከረረ ግጭት ውስጥ ሲገባ በመካከላቸው ያለው ቅራኔ የሚታረቅ ነው? ወይስ የማይታረቅ? ብለን መጠየቅ አለብን። የሚታረቅ ከሆን የከረረ ግጭት የምንለው መለስተኛ በሆነ ወይም በቀላሉ በሽማግሌ፣ በድርድር በተለያየ መንገድ ሊፈታና ያ ጊዜያዊ ውጥረት ረግቦ ዘላቂ ምፍትሄ ያገኛል። የማይታረቅ ቅራኔ ውስጥ ሲገባ ግን አንደኛው ሌላውን በጉልበት ያለፍላጎቱ አንቆ ይዞታል ማለት ነውና፣ የጉልበት ጫና የደረሰበት የተበደለው ወገን ወደ እምቢተኛነት ሄዶ አልገዛም ይላል፣ ይህ የመጨረሻው የፍጥጫ ደረጃ ስለሆነ በሁለቱ ተቃራኒ ሀይሎች መካከል ያለው ግብግብ መፍተሔ የሚያገኘው፣ ተጨቋኙ ጨቋኙን አውርዶ የራሱ የሆነ ህዝባዊ*

*ዴሞክራሲያዊ የአንድነት መንግስት ሲመሰርት እና የሚፈልገውን ማድረግ ሲችል ብቻ ነው። ስለሆነም የማይታረቅ ቅራኔ የሚፈታው በተለያየ መንገድ ጉልበት ማሳየትን ያካተተ ይሆናል። ይህ ማለት ደግሞ ተወደደም ተጠላም ያለውን መንግስት አለመቀበልን ህገመንግሰቱን፣ መጣስን የግድ ይላል። ይህ በሚደረግበት ወቅት መንግስትም ሕዝብን ከማሰቃየትና ከመግደል ወደኋላ እንደማይል በስነ ልቦና ግንዛቤ ብቻ አንስተን በትንታኔ ለማስረዳት የምንሞክረው ጉዳይ ሳይሆን በተጨባጭ ወያኔ እያሳየን ያለው ሁኔታ ከቲዎሪ ተነስተን የወያኔን ምንነት ለማሳየት ከምንጥረው የበለጠ ህዝባችን ጠዋትና ማታ የሚኖርበት ኑሮ በግላጭ ያሳየናል። ነገር ግን ይህን መሰረታዊ ሀቅ በውል ያጠናነው አይመስልም።*

1) *ቅራኔው ይታረቃል ካልን ወያኔን የምንቃወምበት መንገድ ህገምነግስቱን በማክበር ወያኔንም እነደ ህጋዊ መንግሰት ተቀብለን ማንኛውም ህጋዊ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ ማድረግ እንዳለበተ ሁሉ ፖሊሲዎችን በመቃዎም ደረጃ ተወስነን ወቅቱን ጠብቆ ለሚምጣው ምርጫ በየ እርከኑ መሳተፍ አከራካሪ አይሆንም።*

2) ቅራኔው ግን የማይታረቅ ነው ስንል ከወያኔ ጋር የምንተያየው በጠላትነት መሆኑ በጣም ግልፅ ሆኖ መቀመጥ አለበት።በኢትዮጵያ ህዝብና በወያኔ መካከል ባለው ሁኔታ የወያኔ መንግስት ህገ ወጥና ህገ መንግስቱም የኢትዮጵያን አንድነትና ህልውና የሚፃረር ጠባብና የአንድን ጎሳ ጥቅም የማያስጠብቅ ስለሆነ በማንኛውም መንገድ የወያኔን መንግስት ደምስሶ ህገ መንግስቱ አፍርሶ፣ የአዲሲቱን ኢትዮጵያ አንድነት የህዝቡን ጥቅምና ዴሞክራሲያዊ መብት እንደሚያስከብር ሆኖ ህገመንግስቱ እንደገና መደንገግ ይኖርበታል።

ወደድንም ጠላንም ከዚህ ሀቅ ልንሸሽ ስለማንችል ጥያቄው መልሶ መላልሶ ይመጣል። አሁንም ወጥሮ የያዘን ይኸው ቅራኔ ሲሆን ሳይንሳዊ መፍትሄ ልንሰጠው ባለመቻላችን በተቃዋሚ ድርጅቶች መካከል ክፍተትን እንደፈጠረ ተቀምጧል። ወያኔን በጠላትነት ስንፈርጀው ህዝባዊ ትግሉ ወያኔን ጨርሶ መደምሰስ ብቻ ሳይሆን የተጋድሎ ሀርነት ህዝብ ትግራይ ድርጅት እንደ ማንኛውም የፋሽስት ድርጅት ህገ ወጥ የሚሆንበት ትግል መሆኑን ማወቅ አለብን።ይህን ለማድረግ ወያኔ ስልጣኑን በቀላሉ እነደማይለቅ ካለፈፉት አመታት ታሪኩ መረዳት አዳጋች እንዳልሆነ ግልፅ ነው፣ እዚህ ላይ አስረግጠን ማወቅ ያለብን የቅራኔውን አይነት ብቻ ሳይሆን ይዘቱንም ጭምር ይሆናል። ከዚህም በመነሳት ህዝቡ በቃኝ ሲል የቅራኔው ውልድ የሆኑ ህዝባዊና ሀገራዊ የፖለቲካ ድርጅቶች መፈጠራቸው እሙን ነው። ነገር ግን እንደዚህ ባለ ቀውጢ ቀን የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች እንደአሸን ይፈላሉ። ይህ ደግሞ በኢትዮጵያ ላይ ብቻ የተከሰተ ሳይሆን በብዙ ሀገሮች የታየ ነው።በዚህ ሁኔታ የኛ ሚና ከምጊዜውም በበለጠ ለህዝባዊ ትግሉ አለኝታና ተስፋ በመሆን ታላቅ አስተዋፅኦ ሊያደርግ መነሳት ያለበት።

ይህን ታላቅ ሃላፊነት ለመውሰድ ህዝባዊ ወታደርም ለመሆን እስከአሁን ድረስ ባደረግናቸው የትግል ተሳትፎዎች ትግሉ የሚጠይቀውን ግንዛቤ ይዘን ነው ድርጅቶችን የምንደግፈው/የምንቃወመው? ወይስ ቅዱሳን መላእክት የድርጅት መሪዎች ፅፈው ያነበቡልንን ስፋቱንና ጥልቀቱን ሳንመረምር በእምነት ብቻ ወያኔን እስከ ታገሉ ድረስ ከሚል ቅን መንፈስን በመመርኮዝ ነው አባልና ደጋፊ ሆነን የምንሄደው? እስከ መቸ ድረስ ነው አወድሱ ያሉንን ስናወድስ፣ አውግዙ ያሉንን ስናወግዝ የምንኖረው?

ከላይ የተነሱትን መሰረታዊ የቅራኔ አይነቶችን በቅድሚና በቅጡ ካልተረዳን የጠለቀ የትግል ግንዛቤ ከሌለን ቅራኔው በፈጠራቸው ህዝባዊ ድርጅቶች አምሳያ ተመስለው አድርባይና የጠላት ወገን የሆኑ የፖለቲካና ማህበራዊ ድርጅቶች ጎን ለጎን ስለሚፈጠሩ፣ በነዚህ የጠላት ወገን በሆኑት አስመሳይና ቀጣፊ ድርጅቶች መሰለባችን ሳይታለም የተፈታ ነው። የምንፈልገው ቃል ያሰሙናል የምንጮኸውን ጩኸት ሲያስተጋቡልን ወገን ማለት ይህ ነው ብለን ከመከተል የሚያቆመን ከአስተሳሰብ የመነጨ መመሪያና ቅድመ ዝግጅት የለንምና እንደ አሁኑ ቀቢጸ-ተስፋ ሆኖብን ያዙን ልቀቁን ከማለት ያለፈ ቢኖር ጅብ ከሄደ ዉሻ ጮኸ ነው።

ኢትዮጵያችን ብለን የተነሳንበት የአንድነትና የዴሞክራሲ ትግል መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት ከሆነ፣ እኛ እራሳችን መሰረታዊ የአስተሳሰብ ለውጠ ማድረግ አለብን። አለበለዝያ እኛም ቃጭል ጩኸታችንም የገደል ማሚቶ ይሆናል ሆኗልም።

የኢትዮጵያ ህዝብ መስከረም 1998 ዓ/ም አዲስ አበባ ላይ የቅንጅትንና የህብረትን አመራሮች ፓርላማ አትገቡም ብሎ ሲቃወምና ሲያግታቸው፣ ከወያኔ ጋር ያለውን ቅራኔ በግብግብና በአመፅ እንጅ በፓርላማ ውድድርና ድርድር እንደማይፈታ አበክሮ የተረዳው በመሆኑ ነው። እኛ ከኢትዮጵያ ህዝብ በ አምስት አመት ወደ ኋላ ቀርተናል ብንል ስህተት አይሆንም።ስለሆነም እዚህ እንደ

ምናስበውና እንደምንመኘው ሳይሆን፣ ህዝባችን እኛና አለኝታ ብለን ከምናንጨበጭብላቸው ድርጅቶች ልቆና ተመንጠቆ ከወያኔ ጋር የበላ አፈር ይብላ ስለአለ ነው 97 ላይ ወግዱ ብሎ እነ ልደቱን የተፋቸውን፣ የዛሬውንም  አቶ ሃይሉ ሻወል ሀየሎም ሻወል ብሎ የተዛበተበት። እነዚህን መሪዎች ለተምሳሌ አነሳን እንጅ ህብረትና ቅንጅት ከተሰነጣጠቁ ወዲህ የጠራ አመለካከት ሳይኖራቸው መተከላቸው ምን ላይ እንደቆመ ግልፅ ሳይሆን በፕሮፓጋነዳ መርህ ብቻ የተለመደ ፈሊጥ ሆኖ <u>የሰላም ትግል፣</u><u>ሁለ ገብ ትግል፣</u> <u>የትጥቅ ትግል፣</u> ሲባል እንሰማለን። እነዘህ የትግል መርሆች በውስጣቸው ሰፋ ያለ ይዘት አላቸው። እኛም ሆን የምንከተላቸው ድርጅቶች እያንዳንዱን የትግልመርህ እንስተው ተወያይተው አንደኛውን  ከሌላኛውን ለምን እንደመረጡት ተረድተን ሳይሆን  በድርጅቱ ከተመረጠ ዘንዳ፣ ብለን ተገቢውን ጥያቄ ሳንጠይቅ፣ ለመሆኑ ይህ የያዝኩት የትግል ዘዴ ከምን የመነጨ ነው? ድርጅቴስ ለምን ይህን መንገድ መረጠ? ሳንል የተሰጠንን መርህ እንግበን ታጋይ ነን ስንል እንገኛለን። ሰለሆነም ትግሉ አሁን ያለበት አሳዛኝ ደረጃ ላይ ይገኛል። ታዲያ የጥፋቱ ተካፋይ አይደለንም ለማለት እንችላለን?

ትግሉ አቸናፊ እንዲሆን ወደ ትግሉ መቀላቀል የግድ ነው ስንል እንዲሁ ባገኘሽው ተቀላቀል ማለት አይደለም። ከወያኔ ጋር ያለው ትግል አንድ ጠዋት በክርኒ ጅርባዉን ሰብረን የምገላገለው አይደለም። ብዙ ውጣ ውረድ ያለው} ከገንዘብና ከጉልበት አልፎ ህይወትንም የሚጠይቅ ስለሆነ በቅድሚያ በትግሉ ላይ የጠራ አመለካከት ከሌለን የምንቀላቀላቸውንም ድርጅቶች ካለን የሀገር ፍቅርና ቅን ፍላጎት የተነሳ ብቻ ስለሚሆን እንደ በግ ሲነዱን ይኖራሉ።; በአስተሳሰብም የበሰልን ስላልሆንን ድርጅቶችን ከመጎዳኘታችን ብፊት ተገቢውን ጥያቄ ለማንሳት አልቻልንም። በመሆኑም ለመፍረሳቸውም አስተዋጽኦ አድርገናል ብንል ስህተት አይሆንም።

ድርጅቶች የሚታመኑትና የሚለኩት የሚከበሩት በአባሎቻቸው ጥንካሬ ነው። ምክያቱም ቢባል የድርጅቱ ሃዋሪያዎች አስተማሪዎች አደራጅዎች ቀስቃሾች አባላቱ ናችውና።የማንኛውም ድርጅት አመራር ጥንካሬ የሚመዘነው አባለቱን በትጋት የሚአስተምርበትና የሚያሳትፍበት ወቀሳንም እንደፀጋ የሚቀበል ለመማርም ዝግጁና ጥሩ አዳማጭ ሲሆን ነው። ከነዚህ ሀቆች የሚርቅ ድርጅት መጨረሻው ውድቀት ነው። እኛም አብረን አሁን እንደወደቅነው ሁሉ ሁልጌዜም ስንወድቅ ስንነሳ እንኖራለን። የሰለጠነ ፖለቲካ የሚሉን እስከዚህ ድረስ መሆኑን መረዳት ይኖርብናል። የሀገርና የህዝብ እንጅ የድርጅት ውለታ የለብንም።; ወያኔን ጠላት ማለት ካልቻልን ከነልደቱና ከነ ሀይሉ ሻወል ከመሰሎቻቸው ጋር ሆነን መቀጠል ይኖርብናል። ወያኔ ጠላታችን ነው ካልን ደግሞ ጠላትነቱን ይፋ አድርገን የድርጅት ፕሮግራማችንን በዚያው አንፃር አስተካክለን የምንከተለውን የትግል ዘዴ ከነምክኒያቱ አስረግጠን ለሚከፈለው መስዋት ተዘጋጅተን መነሳት ይኖርብናል። ሌላ ምርጫ የለንም። ጩኸቱ እዚሁ ላይ ቢቆምና እራሳችንን በተገቢዉ አስተሳሰብ እያነፅን ትግሉን መግፋት ይጠበቅብናል። በጩኸ ት በንዴት የምናጠፋውን ጊዜና ሀይል <u>የጎደለንና ያጣነውን  ግንዛቤና (CLARITY)</u> <u>ጥራት</u> መሆኑን አውቀን ለትግል ከመደብነው ጊዜ ከፊሉን በንባብ በጥናትና በምርምር በጤነኛ ውይይት እናሳልፈው። እነዚህን መርህ ሃሳቦች ስንከተል ነው ድርጅቶችን በጤነኛ መንገድ ታገሉ ብለን ልንወቅስ የምንችለው። እነሱም አርጉ ሲሉን በደስታ ተቀብለን ፍሬያማ የትግል ውጤትም ለማየትም እንችላለን። <u>በእውቀት</u> ላይ የተገነባ ትግል መሰረት ያለው እምነት ይሰጠናል፣ ፅናትና ቀጣይነት የትግል ባህላችን ይሆናል። የኢትዮጵያ ህዝብ ከኛ ከሚፈልገው አንዱ ባህሪ ይህ ነው። ይህም የድርጅቶቸን ግልፅነት የኛንም ንቃተ ህሊና ያበለፅጋል በሎም የህዝቡ ትግል አቸናፊ ይሆናል።

ኢትዮጲያ በልጆቹዋ ትገነባለች!!!

ከእያዩ ቢወጣ